ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የውበት መጠበቂያ ምርቶች ላይ ቁጥጥር ማድረግ ለምን አስፈለገ ?

በምግብና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/11 የውበት መጠበቂያ ምርቶችን ምንነት በሚመለከት ግልፅ ማብራሪያ ተቀምጧል። በአዋጁ "የውበት መጠበቂያ ምርት" ማለት በማሸት፣ በማፍሰስ፣ በሙቀት በማቅለጥ፣ በመንፋት፣በመርጨት ወይም በተመሳሳይ መንገድ በገላ ወይም በሰውነት ክፍል ላይ የሚደረግ ሰውነትን ለማጽዳት፣ ለማስዋብ፣ ደምግባት ለመጨመር ወይም የአካልን ቅርጽና አሠራሩን ሳይቀይር ገጽታን ለመቀየር የሚውል ምርትና ለውበት መጠበቂያ ምርት ጥሬ ዕቃነት የሚውል መሆኑ ተመላክቷል።

ይሁንና የላውንደሪ ሳሙናዎችን፣በሽታን ለመከላከል፣ ለመመርመር፣ ለማከም ወይም ለመፈወስ ታስበው ጥቅም ላይ የሚውሉና በማንኛውም ሰው የሰውነት የተፈጥሮ ቅርጽ ወይም የአሰራር ሂደት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ምርቶችን እንደማያካትትም ተቀምጧል።

ከዚህም ባሻገር በገበያ ላይ የሚውል ማንኛውም የውበት መጠበቂያ ምርት በተገቢ ወይም በተለመደ አጠቃቀም በሚወሰድበት ወቅት በሰው ጤና ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆን እንደሌለበትና ማንኛውም የውበት መጠበቂያ ምርት አምራች፣ አስመጪና አከፋፋይም በባለስልጣኑ መመዝገብ እንዳለበት በግልፅ ተቀምጧል።

የውበት መጠበቂያ ምርት ስለማሳወቅና ይዘቱን በተመለከተም፣ማንኛውም ሰው የውበት መጠበቂያ ምርት ማምረት ወይም ለንግድ ወደ ሀገር ማስመጣት የሚችለው የውበት መጠበቂያውን ዝርዝርና ተያያዥ መረጃ አስፈጻሚ አካሉ በሚያዘጋጀው አሰራር መሠረት ሲያሳውቅ ብቻ እንደሆነና ማንኛውም የውበት መጠበቂያ ምርት የተከለከለ ንጥረ ነገር መጨመር ወይም ተፈጻሚነት ባለው መስፈርት መሠረት ከተፈቀደ የንጥረ-ነገር ይዘት መጠን በላይ ሊኖረው እንደማይገባም ተደንግጓል።

የውበት መጠበቂያ ምርት ስለማምረት፣ ስለማከማቸት፣ ስለማጓጓዝና ስለመሸጥ በተመለከተ ደግሞ ማንኛውም አምራች የሚያመርተው የውበት መጠበቂያ ምርት የመልካም አመራረት ሥርዓትን በተከተለ መልኩ መመረቱን ማረጋገጥ እንዳለበት እንዲሁም ማንኛውም አምራች፣ አስመጪ፣ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ምርቱ ደህንነቱን በማያጓድል መልኩ የማምረት፣ የማከማቸት፣ የማጓጓዝ ወይም የመሸጥ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ይገልፃል። አምራች ወይም አስመጪ ድርጅትም ከምርቱ ደህንነት ችግር ጋር ተያይዞ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት መውሰድ እንዳለበት ይደነግጋል።

ይህን አዋጅ ወይም ሌላ ተፈጻሚ የቁጥጥር መስፈርቶችን የማያሟላ የውበት መጠበቂያ ምርት ወይም የምርት ጥሬ ዕቃ ማምረት፣ ማስመጣት፣ ማከማቸት፣ ማከፋፈል፣ ማጓጓዝ ወይም መሸጥ እንደማይቻልና ከማንኛውም ከምርት ጋር ንክኪ የሚኖረው ማከማቻና ማጓጓዣ ዕቃ ንጽህናው የተጠበቀ ሆኖ ምርቱን ለማንኛውም ኬሚካላዊ፣ አካላዊ ወይም ማክሮባይሎጂካል ብክለት የማያጋልጥ መሆን እንደሚኖርበት አዋጁ ያሳስባል።

የውበት መጠበቂያ ምርቶች (ኮስሜቲክስ) ከቆዳ እንክብካቤና ከግል ንፅህና ጀምሮ ውበትና በራስ መተማመንን እስከማሳደግ ድረስ በሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ጉልህ ሚና የሚጫወቱ ቢሆንም ደህንነታቸው ያልተጠበቁ ወይም ጥራት የሌላቸው የውበት መጠበቂያ ምርቶች ግን የመጉዳት እድላቸው ከፍተኛ ነው። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ሕብረተሰቡን ከእነዚህ ምርቶች ጋር ተያይዘው ከሚመጡ አደጋዎች ለመከላከል የመዋቢያ ምርቶችን በመቆጣጠር ረገድ የተለያዩ የቁጥጥር መመሪያዎችን ጭምር በማዘጋጀትና የቁጥጥር ስራዎችን በመመሪያው መሰረት ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ ይገኛል።

ባለስልጣኑ የውበት መጠበቂያ ምርቶችን የሚቆጣጠርበት አንዱና ዋነኛው ምክንያት የሸማቾችን ደህንነት ለማረጋገጥ ነው። በተለይም የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች በምርቱ ላይ እንዳይኖር፣ጥራትና ደህንነታቸውን ጠብቀው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ነው።

የምርቶች ጥራትና ደህንነታቸው ካልጠበቀ እንዲሁም ጎጂ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን ከተካተቱባቸው የቆዳ መቆጣትን፣ አለርጂዎችን ወይም የረዥም ጊዜ የጤና ጉዳዮችን እንደ ካንሰር ወይም የመራቢያ ጉዳትን ኢንፌክሽንና ሌሎች አሉታዊ ውጤቶች ሊያስከትሉ ይችላሉ። የውበት መጠበቂያ ምርቶችን ቁጥጥር ስራ የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች እንዳይኖሩ፣ ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሁም መርዛማ ያልሆኑ ምርቶች በገበያ እንዲኖሩና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

በባለስልጣኑ የውበት መጠበቂያ ምርቶችን መቆጣጠር ያስፈለገው ሌላው ወሳኝ ጉዳይ ሁሉም የውበት መጠበቂያ ምርቶች የጥራት ደረጃዎችን እንዲያሟሉ ማረጋገጥ ነው። ለምሳሌ፣ ደረጃቸውን ያልጠበቁ የውበት መጠበቂያ ምርቶች ከመጠን በላይ የከባድ ብረቶች፣ ያልተፈቀዱ ኬሚካሎች ወይም ጥቃቅን ተህዋሲያን በውስጣቸው ሊይዙ ይችላሉ። ጥራት የሌላቸው ምርቶች የሚጠበቅባቸውን ጥቅም አለመስጠት ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የጤና ጉዳት ሊያስከትሉም ይችላሉ።

የባለስልጣኑ የቁጥጥር ማሕቀፍ አምራቾች ከንጥረ ነገሮች ምንጭ እስከ የተጠናቀቁ ምርቶች ማሸግ ጥብቅ የጥራት ቁጥጥር እርምጃዎችን መከተላቸውን ያረጋግጣል። ይህ መመዘኛ የምርቱ ጥራትና ደህንነት ክትትል ስራ በማጎልበት በተጠቃሚዎች መካከል መተማመንን ይፈጥራል። አስተማማኝ የገበያ ልውውጥም ያጎለብታል።

ኢትዮጵያ እንደ ሌሎች ታዳጊ ሀገራት ለሀሰተኛና ደረጃቸውን ያልጠበቁ የውበት መጠበቂያ ምርቶች ተጋላጭ ናት። የሀሰተኛ የውበት መጠበቂያ ምርት ብዙውን ጊዜ ርካሽ በሆኑ ጎጂ ንጥረ ነገሮች ይመረታሉ። አስፈላጊው የደህንነት ሙከራም አይደረግባቸውም። በመሆኑም ሸማቾችን ጤና እና ሰውነት በአጅጉ ሊጎዱ ይችላሉ።

ባለስልጣኑ የውበት መጠበቂያ ምርቶችን በመቆጣጠር እነዚህን የመሰሉ ሀሰተኛ ምርቶች ወደ ገበያ እንዳይገቡ፣ መደበኛ ቁጥጥር በማድረግና ስርጭታቸውን ለመከላከል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ይሰራል። በዚህም የተጠቃሚዎችን ጤና ይጠብቃል፣ የገበያ ታማኝነትንም ይደግፋል።

የኢንዱስትሪው ዓለም አቀፋዊ ባህሪን ከግምት ውስጥ በማስገባት በርካታ ምርቶች ከተለያዩ አገሮች ወደ ኢትዮጵያ ይገባሉ። ባለስልጣን መስሪያ ቤቱም ምርቶች ወደ አገር ውስጥ ገበያ ከመውጣታቸው በፊት የኢትዮጵያን የጥራት ደረጃ እንዲያሟሉ ያደርጋል። ይህን ማድረግ ፋይዳው ዘርፈ ብዙ ነው።

በተመሳሳይ በኢትዮጵያ ተመርተው ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን ይቆጣጠራል። የአገር ውስጥ አምራቾች ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውንም ያረጋግጣል። ይህም ለአገሪቱ እያደገ ላለው የመዋቢያ ኢንዱስትሪ ያለው ፋይዳ እጅጉን ግዙፍ ነው።

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ መሰል የውበት መጠበቂያ ምርቶች የቁጥጥር ሕግን ተፈፃሚ የሚያደርገው ሰዎች ከደህንነት ስጋት ለመታደግ በአጠቃላይ ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ ማህበረሰብን ለማሳደግ ነው። ቀጣይ ትኩረት ተግባሩም ይህን ኃላፊነት ይበልጥ ማስቀጠል ይሆናል።


Tel : +251-11-552-41-22 | http://www.fmhaca.gov.et/contact/
+251-11-552-41-22 | E-mail contactefda@efda.gov.et
P.o.box. 5681 | Telegram channel link
Free call. 8482 | https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/


በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ